የእስልምና መሰረቶች

ሁለተኛ ክፍል



በሳፊያ ኢቅባል

ትርጉም በአህመድ የሱፍ



የአማርኛ እትም

- የወጣቱ ተልዕኮ
- ኢሜል፡ ahmedyesuf29@gmail.com
- ዌብሳይት፡ www.youth-mission.com

የእስልምና መሰረቶች

የእስልምና ጥናቶች የመማሪያ መጽሐፍ

ሁለተኛ ክፍል



በሳፊያኢቅባል

MA, MA, B,Ed

ትርጉም በአህመድ የሱፍ

© አል-አስር ህትመት

በዚሁ ደራሲ የተዘጋጁ ሌሎች መጽሐፍት፡-

- የእንግሊዘኛ ግጥም መማሪያ መጽሐፍት
- ሪትም ከክፍል 1 እስከ 9

የእስልምና ጥናቶች መማሪያ መጽሐፍት፡-

- የእስልምና መሠረቶች፡ ከክፍል 1 እስከ 8 + የእስልምና መጀመሪያ እና መዋዕለ ህፃናት-መጀመሪያ

የማኅበራዊ ጥናቶች መማሪያ መጽሐፍት፡-

- የዓለም ታሪኮች፡ ከክፍል 1 እስከ 6
- ሴቶች እና የእስልምና ሕግ

ዓለም አቀፍ አከፋፋዮች፡-
አል-ሙታናቢ መጽሐፍ ቤት፣ ዱባይ፣
የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ

ስዕላዊ መግለጫ፡- ሲዛር ቦቴ

ንድፍ እና አቀማመጥ፡- ፊውቸርን ፕራይም፣ ዱባይ

- የመጀመሪያ እትም፡ 1996
- ሁለተኛ እትም፡ 1997
- ሦስተኛ እትም፡ 2010



አሳታሚ

- አል-አስር አሳታሚ
- ኢሜል፡ salabbhai@emirates.net እና dawood@mutanabbi.com

መቅድም

ይህ የጀማሪዎች የእስልምና መጽሐፍ ለመረዳት ቀላል ፣ ሳቢ እና ማራኪ በሆነ አቀራረብ ተዘጋጅቷል። ይህ የጀማሪዎች መጽሐፍ ተማሪዎች ሁሉንም የእስልምና ሁኔታዎች እንዲያዩ እና እንደ አንድ የህይወት መንገድ እንዲቀበሉ ይረዳል። እስልምና በህይወት ላይ ያለውን ተፅእኖ በጠቅላላ ያሳያል።

መጽሐፉ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ህይወታቸው ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ መመሪያ ነው። በተለያዩ ደረጃ እና የህይወት እርከን ላይ ላሉ ልጆች የትክክለኛ ባህሪ እና ስብዕና መመሪያ ነው። ይህ መጽሐፍ የተማሪዎችን ባህሪ ያስተካክላል። በትምህርት ህይወታቸው ጥሩ ጓደኛቸው ሊያደርጉት እንደሚችሉ ተስፋ አደርጋለሁ።

ይህ መጽሐፍ የአድርግ እና አታድርግ ትዕዛዞች የሚቀርቡበት ብቻ አይደለም። ባህርያቶችን እና ልማዶችን ያስተካክላል ጥሩና በጎ ስብዕናን የሚገነቡ ትምህርቶችን አጠቃሎ ይዟል። ለአስተማሪዎች እና ለወላጆች ጥሩ የማስተማሪያ መጽሐፍ ነው።

የዚህ መጽሐፍ ስኬት የሚወሰነው በአስተማሪዎች እና በወላጆች እያንዳንዱን ሃሳብ በጥልቀት ከተማሪዎች ጋር በመወያየት መረዳታቸውን ፣ መቀበላቸውን እና መፈፀማቸውን በማረጋገጥ ነው። የመማር ማስተማር ሂደቱ ማወቅን ፣ መረዳት ፣ መቀበል እና በሃሳቡ ላይ መስራት ወይም መፈፀምን ያጠቃልላል። የእያንዳንዱ እውነታ መንፈስ እና መልዕክት በልጆች ስብዕና ላይ ተፅእኖ ሊኖረው ይገባል። እንዲሁም በእለት ተእለት ህይወታቸው ሃሳቡን ወደ ተግባር መቀየር ይኖርባቸዋል።

ኒውደሊ ህንድ ታህሳስ 1997
ሳፊያ ኢቅባል

ለመምህራን

የዚህ መጽሐፍ አላማ ከአምስት እስከ ስድስት አመት እድሜ ላሉ ልጆች የተለመዱ የእስልምና ቃላቶችን ፣ መሰረታዊ ሃሳቦችን እና የግብረገብ ትምህርቶችን ቀለል ባለ መልኩ እንዲገነዘቡ ማስቻል ነው።

ከስድስት እድሜ በታች ላሉ ልጆች በደንብ ማንበብ ላይችሉ ይችላሉ። ሆኖም ይህ መጽሐፍ ትንሽ ፅሁፎችን እና ብዙ ምስሎች ያሉት ሲሆን በመምህራኑ እና በወላጆች ቃላዊ አቀራረብ ላይ የተመሰረተ ነው። እያንዳንዱን ገፅ እንደ አንድ ትምህርት እና ስለአንዷ አረፍተነገር ወይም ሃሳብ ብዙ ማሰራት ይመከራል።

መጽሐፉ ለእያንዳንዱ ቃል በጥያቄና መልስ መልክ ሶስት ትምህርቶችን ይዟል። እነዚህ ትምህርቶች እና ጥያቄዎች ወደ ትምህርት ሊቀየርና ፣ ተያያዥ ሲሆኑ ታሪኮች ሊደገፍ ይገባል። ቀለል ባለመልኩ ስለአንዱ ጥያቄ አንድ ሙሉ ክፍለ ጊዜ ይወያዩበት። ጥያቄና መልሱን በክፍለ ጊዜው መጨረሻ 10 ደቂቃዎች ውስጥ ጥቁር ሰሌዳው ላይ አስፍሩት።

ልጆች አሻንጉሊቶችን ፣ ብሩህ ቀለማትን ፣ አበቦችን ፣ ጣፋጭ ነገሮችን እና የተለያዩ ጨዋታዎችን ይወዳሉ። አዳዲስ ነገሮችን ማየት እና መስራት ፣ አዳዲስ ጨዋታዎችን መጫወት ይወዳሉ። እነዚህን ፍላጎቶች እና የልጆች ዝንባሌ ለማስተማር ልትጠቀሙበት ይገባል። በእያንዳንዱ ትምህርት አሻንጉሊቶችን ፣ ደስ የሚሉ ቻርቶችን ፣ አበቦችን ፣ ጣፋጭ ፍራፍሬዎችን ፣ ጨዋታዎችን ፣ አዳዲስ ነገሮችን ፣ አዳዲስ የማስተማር ዘዴዎችን እነደማስተማሪያ መርጃነት ተጠቀሙባቸው። በእያንዳንዱ ትምህርት አንድ መርጃ መሳሪያ መጠቀማችሁን እርግጠኛ ሁኑ። የማስተማራችሁ ስኬት ማረጋገጫ ይሆናል።

ደስ የሚሉ የሚያብለጨልጩ ፣ ያጌጡ ቻርቶችን ለትምህርቶቹ ጥሩ ቃላቶችን በትልቅ ፊደላት አዘጋጅታችሁ የመማሪያ ክፍል ውስጥ አንጠልጥሉት። ልጆች አበቦችን ይወዳሉ። ትልቅ አበቦችን ሳሉ እና ልክ አሏህ ፣ ነብዩ ሙሐመድ እንደሚሉ ያሉ ቃላቶችን ከአበቦቹ መሃል ፃፏቸው።

በእያንዳንዱ ገፅ ላይ ስላለው ሃሳብ መርጃ መሳሪያዎች በመጠቀም ከልጆች ጋር ከተወያያችሁ በኋላ ትምህርቱን ግልፅ እና ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡት። ከዚያም እንደዚያው ልጆች እንዲያገቡ አድርጉ። ልጆች ሳይገባቸው ፣ ሳይረዱ እንዳያልፉት ጥንቃቄ አድርጉ።

የእስልምና ጥናት ክፍለጊዜያቸውን ደስ የሚል በደስታና በጉጉት የሚጠብቁት ክፍለጊዜ እንደሆን የቻላችሁትን ሁሉ አድርጉ። የተግባር ልምምድ ፈፀሙ በውስጡም የጫዋታ ጊዜ እንዲኖር አድርጉ። ስለ እናት ሐዲስ ስታስተምሩ የስጦታ ካርድ ከአበባ ጋር አዘጋጅታችሁ የመማሪያ ክፍል ውስጥ እያንዳንዱ ልጆች ለወላጆቹ ስጦታውን እንዲሰጡ አድርጉ። የእስልምና ጥናት ክፍለ ጊዜ መሆን ያለበት ከእረፍት ጊዜ በፊት ነው። የእረፍት ጊዜ ለልጆች የደስታ የጨዋታ ጊዜ ነው። የእስልምና ጥናትን ከዚያ ጋር ማያያዝ ደስ የሚል የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ያስችላል።

የጽሁፍ የቤት ስራ ወይም ማስታወሻ ደብተር ሊኖር አይገባም። ፈተና ሊሰጣቸው የሚገባው የቃል ፈተና ብቻ ነው።

መጽሐፍ የተዘጋጀው ትምህርቶቹን በሶስት ክፍሎች በመክፈል ነው። እያንዳንዱ ትምህርት የሚበቃው በጥያቄና መልስ ነው።

የፎቶ ምስሎች እና አጫጭር ቪዲዮችን ለመማር መስተማር ሚሚያነት ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ። በእሱ መተካት ግን አያስፈልግም። ለምሳሌ

ካዕባ ስለሚለው ቃል ስታስተምሩ ለ3 ወይም ለአምስት ደቂቃ ለሚሆን ጊዜ የካባ እና የሐጅ ቪድዮ ልታሳዩ ችላላችሁ።

ውድ መምህር እና ወላጆች ልጆች የሚያዩትን ነገር ኮፒ ስለሚያደርጉ በመጀመሪያ ለልጆቻችሁ እራሳችሁን ሞዴል አድርጉ። ልጆች የሚያዩት ነገር በቀላል እና ወዲያውኑ ስለሚይዙ ልማዶችን ፣ ባህሪያት እና ያነጋገር እና ያረማመድ ስታይላችሁን ላይ ጥንቃቄ አድርጉ። ስለሆነም ይህን የልጆች ዝንባሌ በመጠቀም ለእራሳችሁ ተጠቀሙበት እነሱ ኮፒ እንዲያደርጉ እራሳችሁን በጎ ምሳሌ አድርጉላቸው።

የምታስተምሩትን ግብረገብ እና መልካም ባህሪ እንዲፈፅሙ አድርጉ።

ማውጫ

ትምህርት 1	እነዚህን ቃላት አንብቡ
ትምህርት 2	ተጨማሪ ሌሎች ቃላት
ትምህርት 3	ተጨማሪ ሌሎች ቃላት
ትምህርት 4	የእስልምና ምሰሶዎች
ትምህርት 5	እነዚህን ቃላት የምናነባቸው መቼ ነው
ትምህርት 6	ትርጉማቸውን እወቁ
ትምህርት 7	ሳጥኖቹን ቀለም ቀቡ
ትምህርት 8	ጥያቄና መልስ
ትምህርት 9	የአላህ ስጦታዎች
ትምህርት 10	ሶላት
ትምህርት 11	ዱአ
ትምህርት 12	የአበላል ስርአት
ትምህርት 13	ሰላምታ መለዋወጥ
ትምህርት 14	መልካም ልጅ
ትምህርት 15	አነዚህን ጥያቄዎች መልሱ
ትምህርት 16	ወላጆቼ
ትምህርት 17	መምህሬ
ትምህርት 18	ጓደኞቼ
ትምህርት 19	ነብዩ ሙሐመድ
ትምህርት 20	መልካም ስራዎች
ትምህርት 21	እንግዶቼ
ትምህርት 22	ጎረቤቶቼ
ትምህርት 23	መመለስ ትችላላችሁ
ትምህርት 24	እነዚህን ጥያቄዎች መልሱ

ትምህርት 1

እነዚህን ቃላት አንብቡ

ቢስሚላሂር ረህማኒር ረሂም

بِسْمِ اللهِ الرَّحْمَنِ الرَّحِيْمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ፣ እጅግ በጣም

አዛኝ በሆነው።



ቢስሚላህ (በአላህ ስም)



ኢስላም (እስልምና)



ማሻ አላህ (የፈለገው ሆነ)



ጀዛከላህ (አላህ ምንዳህን ይክፈልህ)



አልሀምዱሊላህ (ምስጋና ለአላህ ይገባው)



አሰላሙ ዓለይኩም (ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን)

ላ ኢላህ ኢለላህ ሙሐመዱ ረሱሉላህ

لَا إِلَه إِلَّا اللهُ مُحَمَّدٌ رَسُوْلُ اللهِ

ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ሙሐመድ

የአላህ መልእክተኛ ናቸው



አላህ



ሙሐመድ

(ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)



ከሊማ

(የላኢላህ ኢለላህ ቃል)



ሱብሃነላህ

(አላህ ከጉድለት ሁሉ የጠራ ነው)



አላሁ አክበር

(አላህ ከሁሉ በላይ ታላቅ ነው)



ሙስሊም

(ለአላህ ታዛዥ የሆነ)

ትምህርት 2

አንዳንድ ተጨማሪ ቃላት

ሶላት (ስግደት)

ሰዉም (ፆም)

ዘካ (ምጽዋት)

ሐጅ

(ወደ መካ የሚደረግ የሐጅ ጉዞ)

ጅሃድ (ትግል)

ትምህርት 3

ተጨማሪ ቃላት



ሐዲስ



ኢማን
(እምነት)

ሸሐዳ

(የእምነት ምስክርነት)


ላ ኢላሀ ኢለላህ መሐመዱ ረሱሉላህ

لَآ اِلٰـــــهَ اِلَّا اللّٰهُ
مُحَمَّدُ رَّسُوْلُ اللّٰه



አስታግፊሩላህ

አላህን ምህረት እጠይቃለሁ።



ፊ አማኒላህ

በአላህ ጥበቃ ስር ያድርግህ



ሰውም

ፆም



ሶላት


ስግደት

ትምህርት 4

የእስልምና ምሰሶዎች

አምስቱ የእስልምና መምሰሶዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. **ሸሐዳ (የእምነት ምስክርነት)**: ከሊመቱ ሸሐዳ"ን በማንበብ እምነትን ማወጅ።
2. **ሶላት (ስግደት)**: ሶላት በቀን 5 ጊዜ የሚሰገድ ስግደት ነው።
3. **ዘካ (ምፅዋት)**: ግዴታ የሆነ የድሆች መዋጮ ነው።
4. **ሰዉም (ፆም)**: በረመዳን ወር መጾም ነው።
5. **ሐጅ**: ወደ መካ የሚደረግ የሐጅ ጉዞ።



አምስቱ የእስልምና መምሰሶች

ሸሐዳ

ሶላት **ፆም**

ዘካ **ሐጅ**

አምስቱ የእስልምና መምሰሶች

1. ሸሀዳ
2. ሶላት
3. ዘካ
4. ሰዉም
5. ሐጅ

ማስታወሻ፡ ውድ መምህር እና ወላጅ ከላይ የተጠቀሱትን ምሰሶዎች አብራሩላቸው፡፡

ትምህርት 5

እነዚህን ቃላት መቼ እንጠቀማለን?

ሥራ ከመጀመሬ በፊት **ቢስሚላህ** እላለሁ።

ጥሩ ዜና ስሰማ **ሱብሃነላህ** እላለሁ።

ፈተና ሲገጥመኝ እና ስቸገር **ያ አላህ** እላለሁ።

ሲያስነጥሰኝ **አልሐምዱሊላህ** እላለሁ።

አንድን ነገር ሳደንቅ **ማሻ አላህ** እላለሁ።

ስጸጸት **አስታግፊሩላህ** እላለሁ።

የሆነን ሰው ስሰናበት **ፊ አማኒላህ** እላለሁ።

አንድን ሰው ሳመሰግን **ጀዛከላህ** እላለሁ።

ሰዎችን ሰላም ስል **አሰላሙ ዓለይኩም** እላለሁ።



ትምህርት 6

ትርጉማቸውን እወቁ

ቢስሚላሂ ረህማኒ ረሂም ማለት፡- በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ፣ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው ማለት ነው።

ከሊማ (ላ ኢላሀ ኢለላህ ሙሐመዱ ረሱሉላህ) ማለት፡-

ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው ማለት ነው።

አላሁ አክበር ማለት፡- "አላህ ታላቅ ነው" ማለት ነው። የአላህን ታላቅነት ስገልፅ፣ **አላሁ አክበር** እላለሁ።

አላህ አንዱ እና ብቸኛው አምላክ ነው።

ሙስሊም ማለት አላህን የሚታዘዝ ነው። እኔ ሙስሊም ነኝ። አናንተም ሙስሊም ናችሁ።

ሃይማኖቴ እስልምና ነው።

ነብዩ ሙሐመድ የመጨረሻው የአላህ መልዕክተኛ ናቸው።

ሐዲስ የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግሮች ማለት ነው።

ኢማን በአላህ ማመን እና እስልምናን መቀበል ማለት ነው።

ጅሐድ እስልምናን ለማስፋፋት እና በጎነትን ለማስፋፋት በአላህ መንገድ የሚደረግ ትግል ወይም ጥረት ማለት ነው።

ትምህርት 7

ሳጥኖቹን ቀለም ቀቡ

መልሶቹን ሳጥኖቹ ውስጥ በመፃፍ ሳጥኑን ቀለም ቀቡ

1. አንድ ስራ መስራት ስትጀምሩ ምን ትላላችሁ?

2. የሆነ ሰው ሰላም ስትሉ የምትሉት ምንድን ነው?

3. ስታነጥሱ ምንድነው የምትሉት?

4. መልካም ነገር ስትሰሙ ምንድነው የምትሉት?

5. የሆነ ነገር ስታደንቁ ምን ትላላችሁ?

6. በችግር ውስጥ ስትሆኑ ምን ትላላችሁ?

7. ተውበት (ንሰሃ) ስታደርጉ ምን ትላላችሁ?

8. ቻው ስትሉ ምንትላላችሁ?

9. የሆነን ሰው ስታመሰግኑ ምን ትላላችሁ?

10. ከመተኛታችሁ በፊት ምን ትላላችሁ?

ቢስሚላህ

አልሐምዱ ሊላህ

ጀዛከላህ

አስተግፊሩሏህ

አሰላሙአለይኩም

ፊአማኒላህ

ከሊማ

ማሻአሏህ

ያ አላህ

ትምህርት 8

ጥያቄዎች እና መልሶች

ጥያቄ፡ ምንድ ነህ?
መልስ፡ እኔ ሙስሊም ነኝ።

ጥያቄ፡ የፈጠረህ ማነው?
መልስ፡ የፈጠረኝ አላህ ነው።

ጥያቄ፡ ሃይማኖትህ ምንድን ነው?
መልስ፡ ሃይማኖቴ እስልምና ነው።

ጥያቄ፡ ነብይህ ማነው?
መልስ፡ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ነብየ ናቸው።

ጥያቄ፡ ከሊማን አንብብ
መልስ፡ ላኢላሃ ኢለሏህ ሙሐመድ ረሱሉሏህ

ጥያቄ፡ ምን ማለት ነው?
መልስ፡ ከአሏህ ውጭ በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ የለም ሙሐመድ የአሏህ መልዕክተኛ ናቸው ማለት ነው።

ጥያቄ፡ ስንት አምላክ አለ?
መልስ፡ አንድ አምላክ ብቻ አለ።

ጥያቄ፡ ቅዱስ መጽሐፍህ የትኛው ነው?
መልስ፡ ቅዱስ መጽሐፌ ቁርአን ነው።

ጥያቄ፡ ቁርአን ለማን ወረደ (ተገለጠ)?

መልስ፡ ቁርአን የተገለጠው ወይም የወረደው ለነብዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ነው።

ጥያቄ፡ ሙስሊም ማነው?

መልስ፡ ሙስሊም ማለት አላህን የሚታዘዝ እና አሏህን ሚገዛ ሰው ነው።

ጥያቄ፡ መላእክት እነማን ናቸው?

መልስ፡ መላእክት ከብርሃን የተፈጠሩ የአላህ አገልጋዮች፤ የአሏህ ባሮች ናቸው።

ጥያቄ፡ የመጀመሪያው ነብይ ማነው?

መልስ፡ አደም (ዓለይሂ ሰላም) የመጀመሪያው ነብይ ናቸው።

ጥያቄ፡ የመጨረሻው ነብይ ማነው?

መልስ፡ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የመጨረሻው ነብይ ናቸው።

ጥያቄ፡ ነብይ አምላክ መሆን ይችላል?

መልስ፡ ነብይ አምላክ መሆን አይችልም።

ጥያቄ፡ ጀነት ምንድን ነው?

መልስ፡ ጀነት ለጥሩ ሰዎች የተዘጋጀች ደስ የሚል የደስታ ሐገር ነው።

ጥያቄ፡ ጀሐነም (ገሃነም) ምንድን ነው?

መልስ፡ ጀሐነም ለመጥፎ ሰዎች የተዘጋጀች መጥፎ መኖሪያ ቦታ ነው።

ጥያቄ፡ የእስልምና ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ፡ እስልምና ማለት የራስን ፍላጎት እና ፈቃድ ለአሏህ በማስገዛት እና አላህን በመታዘዝ የሚገኝ ሰላም ነው።

ጥያቄ፡ መታዘዝ ያለብን ማንን ነው?

መልስ፡ መታዘዝ ያለብን አሏህን እና መልዕክተኛውን ነው።

ጥያቄ፡ አምስቱ የእስልምና ምሰሶዎች ምንድን ናቸው?

መልስ፡

1. ሸሐዳ
2. ሶላት
3. ፆም
4. ዘካ
5. ሐጅ ናቸው።

ጥያቄ፡ የሸሐዳ ፣ የሶላት ፣ የዘካ ፣ የፆም እና የሐጅ ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ፡

ሸሐዳ፡ ማለት የእምነት አዋጅ ወይም ቃልኪዳን ማለት ነው።

ሶላት፡ በቀን አምስት ጊዜ መስገድ ነው።

ዘካ፡ የድሆች መዋጮ ነው።

ሰውም፡ የረመዷን ወር መፆም ነው።

ሐጅ፡ መካ ውስጥ የሚገኘውን ካዕባ መጎብኘት ነው።




ጥያቄ፡ ሐዲስ ምንድን ነው?

መልስ፡ ሐዲስ ማለት የነብዩ ሙሐመድ ንግግር እና ተግባር ነው።

ጥያቄ፡ ኢማን ምንድን ነው?

መልስ፡ ኢማን እስልምናን መቀበል እና በአላህ ማመን ነው።።

አላህ የሚለውን ቃል በአረብኛ ሳጥኖቹ ውስጥ በመፃፉ ቀለም ቀባቸው?

ጥያቄ፡ የቢስሚላሂ ረህማኒ ረሂም ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ፡ ቢስሚላሂ ረህማኒ ረሂም ማለት በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው ማለት ነው።።

ጥያቄ፡ የአላሁ አክበር ትርጉም ምንድን ነው?


መልስ፡ አላሁ አክበር ማለት አላህ ሃያል ነው ማለት ነው።።

ጥያቄ፡ የላኢላሃ ኢለላህ ሙሐመዱ ረሱሉላ ትጉም ምንድን ነው?

መልስ፡ ላኢላሃ ኢለላህ ማለት ከአላህ ውጭ በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ የለም፤ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ማለት ነው።።

ትምህርት 9
የአሏህ ስጦታዎች

አሏህ ብዙ ስጦታዎችን ሰጥቶናል።



አባት




እሳት




ፀሐይ




ጨረቃ




ኾክ




ቁርአን



ወንበርና ጠረንጴዛ



ቋሚ



የቁስል ፕላስተር



ዝናብ



አበባ



ኳስ



አላህ




ሙሐመድ



መስጊድ




ምሽት




ቀን



አበቦች




ፍራፍሬዎች




መጽሐፍት



ጥቁር ሰሌዳ



ጠረንጴዛ



መምህር



እናት

ትምህርት 10

ሶላት



ሙስሊም ሰው ይሰግዳል።

ሙስሊም ሰው በየቀን አምስት ጊዜ ይሰግዳል።

እኔ በየቀን አምስት ጊዜ እሰግዳለሁ።

ሶላት ከአላህ የተሰጠን ስጦታ ነው።

ስግደት በአረብኛ ሶላት ተብሎ ይጠራል።


አምስቱ የሶላት ስሞች፡

- ፈጅር: የንጋት ሶላት።
- ዙህር: የቀትር ሶላት።
- አስር: የቀትር በኋላ ሶላት።
- መግሪብ: የምሽት ወይም የጥልቀተ ፀሐይ ሶላት።
- ኢሻ: የለሊት ሶላት።

ሶላት አንዱ የእስልምና ምሰሶ ነው።



እሰግዳለሁ። ያለ ሶላት ጥሩ ሙስሊም መሆን አልችልም።



አምስቱ ሶላቶች ሚከተሉት ናቸው።

1. ፈጅር
2. ዙሁር
3. አስር
4. መግሪብ
5. ኢሻ



ትምህርት 11

ዱዓ

ዱዓ ምንድን ነው?

ዱዓ ማለት አላህ የሆነ ነገር እንዲሰጠን መጠየቅ (መለመን) ማለት ነው።

አላህን ስለምን፣

ስኬትን እንዲሰጠኝ ስጠይቀው፣

እርዳታውን ስጠይቀው እና እንዲመራኝ ስጠይቀው

በዱዓ ወይም በጸሎት መልክ ነው።



ሁለት አጫጭር ዱዓዎች፡

رَبِّ زِدْنِي عِلماً

1. **ረቢ ዚድኒ ኢልማ**

ጌታየዋ እውቀትን ጨምርልኝ።

رَبَّنَا اٰتِنَا فِي الدُّنْيَا
حَسَنَةً وَّفِي الْاٰخِرَةِ
حَسَنَةً وَّقِنَا عَذَابَ النَّارِ

2. **ረበና አቲና ፊ ዱንያ ሀሰና፣ ወፊል አኺራቲ ሀሰና፣ ወቂና ዓዛበ ናር**

ጌታችን ሆይ! በምድርም መልካምን ፣ በመጨረሻውም ዓለም መልካምን ስጠን፤ ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን።



ትምህርት 12

የአመጋገብ ስነ-ምግባር



የምበላው በሰዓቱ ነው።

ከመብላቴ በፊት እጆቼን እታጠባለሁ።

ከመብላቴ በፊት **ቢስሚላሂር ረህማኒር ረሂም** እላለሁ።

የምበላው በቀኝ እጄ ነው።

የምበላው በሦስት ጣቶቼ አንስቼ ነው።

ሙሉ ጣቶቼን አላነካካም።

ቀለል ያሉ ምግቦችን እበላለሁ። ወተት፣ ስጋ እና ተምር እወዳለሁ።



የምበላው ቀስ ብዬ ነው፤ በፍጥነት ተቻኩየ አልበላም።

ከሳህኑ መሃል አንስቼ አልበላም።

የምበላው ከፊቴ (ከራሴ በኩል) ካለው ነው።

ምግቡን አላሸትም።

በምበላበት ጊዜ ብዙ አላወራም።

የምበላው እና የምጠጣው ቁጭ ብየ ነው።

ውሃ በምጠጣበት ጊዜ በቀስታ በሦስት ትንፋሽ እጠጣለሁ።

ከተመገብኩ በኋላ፣ ስለ ምግቡ አላህን አመሰግናለሁ።

ትምህርት 13

ሰላምታ መለዋወጥ

ሰውን ሳገኝ "አሰላሙ ዓለይኩም" እላለሁ።

አንድ ሰው "አሰላሙ ዓለይኩም" ሲለኝ ደግሞ "ወዓለይኩሙ ሰላም" እላለሁ።



አንድ ሰው ሲገባ (ለማክበር) ከተቀመጥኩበት አልነሳም፤ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን አይወዱም ነበር።

ወደ ቤቴ ስገባ፣ በቤት ውስጥ ላሉት ሁሉ "**አሰላሙ ዓለይኩም**" እላለሁ።

እንዲሁም የሌሎች ሰዎች ቤት ውስጥ ስገባ **አሰላሙ አለይኩም** እላለሁ።

ያለ ፈቃድ ወደ መማሪያ ክፍል ወይም ወደ ሰው ቤት አልገባም።

ታላላቆቼን እና ልጆችን ሰላም እላለሁ።

ከቤት ወይም ከክፍል ወጥቼ ስሄድ **አሰላሙአለይኩም** እላለሁ።

ሰላምታ ለመለዋወጥ ሌላ ቃል አልጠቀምም።

አሰላሙአለይኩም ብቻነው የምለው።

ሰላምታ የማቀርበው ከፈገግታ ጋር ነው።



ትምህርት 14

ጥሩ ልጅ

የፈጠረኝ አላህ ነው። አላህን እታዘዛለሁ።

አላህ ይወደኛል። እኔም አላህን እወዳለሁ።

ነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) እታዘዛለሁ።



ወላጆቼን እወዳለሁ፤ እታዘዛለሁ።

ሶላቴን እሰግዳለሁ።

ቁርአን አነባለሁ።

ከሰው ጋር አልጣላም። መጥፎ ቃላትን አልናገርም።

ትምህርቴን በደንብ አነባለሁ፤ እፅፋለሁም።

ንጹህ ልብሶችን እለብሳለሁ። ንፅህናየን እጠብቃለሁ።

ለጓደኞቼ ጥሩ ጓደኛ ነኝ።

የሆነ ሰው ሳገኝ **አሰላሙአለይኩም** እላለሁ። የሆነ ሰው ሰላምታ ሲያቀርብልኝ **ወአለይኩም አሰላም** ብየ እመልሳለሁ።

ሳወራ ረጋ ቀስ ብየ እና ግልፅ በሆነ ሁኔታ ነው። ሳወራ አልጮህም።

ከእንቅልፌ ስነቃ ከሊማውን አነባለሁ።

የተለያዩ ነገሮችን ስሰጥ እና ስቀበል በቀኝ እጄ ነው።

ትሁት ነኝ። አንድ ነገር ስፈልግ "እባክህ/ሽ" እላለሁ።

መልካም ነገር ላደረገልን ሰው **"አመሰግናለሁ" "ጀዛከላህ"** እላለሁ።

ለድሆች ሩኅሩህ ነኝ። አዛውንቶችን እረዳለሁ፣ አከብራለሁ።

ጎረቤቶቼን እወዳለሁ።

እንስሳትን አልጎዳም።



ትምህርት 15

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

ጥያቄ፡ ወላጆቻችሁን ትወዳላችሁ ፣ ታከብራላችሁ?
መልስ፡ አዎ ወላጆቼን እወዳለሁ፤ አከብራለሁ።

ጥያቄ፡ የአባታችሁ ስም ማን ነው?
መልስ፡ የአባቴ ስም _____ ነው።

ጥያቄ፡ ወንድ ነህ ወይስ ሴት?
መልስ፡ እኔ _____ ነኝ።

ጥያቄ፡ የምትኖሩት የት ነው?
መልስ፡ የምኖረው _____ ነው።

ጥያቄ፡ የትምህርት ቤታችሁ ስም ማነው?
መልስ፡ የትምህርት ቤታችን ስም _____ ነው።

ጥያቄ፡ እድሜህ ስንት ነው?
መልስ፡ እድሜየ _____ ነው።

ጥያቄ፡ ምታጠኑት የትኛው ክፍል ውስጥ ነው?
መልስ፡ የማጠናው _____

ጥያቄ፡ ቁርሳችሁን ፣ ምሳችሁን እና እራታችሁን የምትበሉት መቼ ነው?
መልስ፡ ቁርስ የምበላው ፣ ሻይ የምጠጣው ጠዋት ነው። ምሳ የምበላው ከሰአት በኋላ ነው። እራት የምበላው ማታ ነው።

ጥያቄ፡ ከእንቅልፋችሁ የምትነቁት መቼ ነው?
መልስ፡ ከእንቅልፌ የምነቃው ንጋት ጠዋት በፈጅር ሰአት ነው።

ጥያቄ፡ የምትተኙት መቼ ነው?

መልስ፡ የምተኛው ማታ ከኢሻ ሶላት በኋላ ነው።

ጥያቄ፡ ነብይ ማነው?

መልስ፡ ነብይ የአላህ መልዕክተኛ ነው። ነብይ መምህር ነው። ከአላህ መመሪያ የተሰጠው ሰው ነው።

ጥያቄ፡ መላኢካ አምላክ መሆን ይችላል?

መልስ፡ አይችልም። መላአክ አምላክ መሆን አይችልም።

ጥያቄ፡ **ሽርክ** ምንድን ነው?

መልስ፡ **ሽርክ** ማለት ለአላህ አጋር ጓደኛ ማበጀት ነው።

ጥያቄ፡ አምስቱ የእስልምና ምሰሶዎች ምን ምን ናቸው?

መልስ፡ አምስቱ የእስልምና ምሰሶዎች

1. ሸሐዳ
2. ሶላት
3. ዘካ
4. ፆም
5. ሐጅ

ጥያቄ፡ የምትከተሉት የትኛውን የአላህ መጽሐፍ ነው?

መልስ፡ የምከተለው ቁርአን ነው።

ጥያቄ፡ ሙስሊም የሆነ ሰው እንዴት አላህ መታዘዝ ይችላል?

መልስ፡ ሙስሊም ሰው አላህን የሚታዘዘው ቁርአን እና ሱናን በመከተል ነው።

ጥያቄ፡ ሱና ምንድን ነው?

መልስ፡ ሱና ማለት የነብዩ ሙሐመድ የህይወት መንገድ ነው።

ጥያቄ፡ ሶላት ምንድን ነው?

መልስ፡ ሶላት ማለት በቀን አምስት ጊዜ መስገድ ነው።

ጥያቄ፡ አምስቶቹ የቀኑ ሶላቶች የትኞቹ ናቸው?

መልስ፡ የፈጅር ሶላት ፣ የዙሁር ሶላት ፣ አስር ሶላት ፣ መግሪብ ሶላት እና ኢሻ ሶላት

ጥያቄ፡ የአላህን ስጦታዎች መጥቀስ ትችላላችሁ?

መልስ፡ የአላህ ስጦታዎች በጣም ብዙ ናቸው። ለምሳሌ ፀሐይ ፣ ጨረቃ ፣ እስልምና ፣ ቁርአን ፣ ነብይ ፣ መስጅድ ፣ ቤት ፣ ወንድምና እህት ፣ የምንጠቀምባቸው ነገሮች በሙሉ።

ጥያቄ፡ ዱአ ምንድን ነው?

መልስ፡ ዱአ ማለት የሆነ ነገር አላህ እንዲሰጠን መለመን ወይም መጠየቅ ነው።

ጥያቄ፡ የሆነ ሰው ስታገኙ በቅድሚያ የምትሉት ምንድን ነው?

መልስ፡ **ሙስሊም** ሰው ሳገኝ **አሰላሙ አለይኩም** እለዋለሁ።

ጥያቄ፡ አሰላሙ አለይኩም ላላችሁ ሰው የምትመልሱለት ምን ብላችሁ ነው?

መልስ፡ **ወአለይኩም ሰላም**

ጥያቄ፡ ንፅህናችሁን የምትጠብቁት እንዴት ነው?


መልስ፡ ገላየን እታጠባለሁ። ጥፍሮቼን እቆርጣለሁ ፣ ፀጉሬን ቅባት እቀባለሁ አበጥራለሁም። ንፁህ ልብሶችን እለብሳለሁ።

ጥያቄ፡ እንዴት ነው የምትበሉት?

መልስ፡ በመጀመሪያ እጃችነን እንታጠባለን፡፡ ቢስሚላህ በማለት በቀኝ እጃችን እንበላለን፡፡ ስንበላ በሶስት ጣታችን ምግቡን አንስተን እንጎርሳለን፡፡ የምንበላው ተቀምጠን ነው፡፡

ጥያቄ፡ ውሃ የምትጠጡት እንዴት ነው?

መልስ፡ ውሃ የምንጠጣው በሶስት ትንፋሽ ጥቂት በመጎንጨት ነው፡፡ ውሃ የምንጠጣው በቀኝ እጃችን ነው፡፡ ከመጠጣታችን በፊት **ቢስሚላህ** እንላለን፡፡ ከጠጣን በኋላ ደግሞ **አልሐምዱሊላህ** እንላለን፡፡ ውሃ የምንጠጣው ተቀምጠን ነው፡፡



ትምህርት 16

ወላጆቼ

እናቴን እወዳለሁ። አባቴን እወዳለሁ።

አከብራቸዋለሁ፤ እታዘዛቸዋለሁም።

ለሚያደርጉልኝ ነገር ሁሉ አመሰግናቸዋለሁ።

በንግግሬ፣ በፈገግታየ እና በመልካም ስራየ ደስተኛ አደርጋቸዋለሁ።





አላማልሳቸውም፤ በፊታቸው ድምፄን ከፍ አድርጌ አልናገርም።

ያለ እነሱ ፈቃድ ምንም ነገር አልሠራም።

ትንሽየ ስጦታዎችን አዘጋጃለሁ፤ ለወላጆቼም ስጦታዎችን እሰጣቸዋለሁ።

እናቴን እና አባቴን አገለግላለሁ።

"ጆነት በእናት እግር ስር ናት።" ስለሆነም እናቴን በጣም እወዳታለሁ፣ አገለግላታለሁ።

ትምህርት 17


መምህሬ

ትምህርት ቤት ውስጥ በጣም ጥሩ መምህር አለችኝ።

መምህሬን አከብራታለሁ። መምህሬን እታዘዛታለሁ።

የመምህሬ ስም እትየ መርየም ነው።

መምህሬ ታስተምረኛለች።



ደስ የሚሉ ታሪኮችን ትነግረናለች።

መጽሐፌን ሳነብ መምህሬ ደስ ይላታል።

መምህሬን አላማልሳትም፤ መጥፎ መልስ አልመልስላትም።

መምህሬ ልክ እንደናቴ ናት።

አንድ ትምህርት ሳልረዳው ስቀር እንድታስተምረኝ እጠይቃታለሁ። ትምህርቱን መልሳ ታስተምረናለች። ትወደኛለች።

ከእኛ ጋር ጨዋታ ትጫወታለች።

ስለታላለቅ ወንድና ሴቶች ታሪኮችን ትነግረናለች። ሁሉም መልካም ሙስሊሞች እንደሆኑ ትነግረናለች።

መምህሬ ፈፅሞ ገርፋኝ አታውቅም።

ለመምህሬ ዱአ አደርግላታለሁ።

መምህሬን እታዘዛታለሁ። በቻልኩት መንገድ እረዳታለሁ።



ትምህርት 18

ጓደኞቼ

ብዙ ጓደኞች አሉኝ።

ለሁሉም ሰው ለጓደኝነት ቅርብ ነኝ።

ያሉኝ ጓደኞች መልካም ናቸው።

ጓደኞቼን በስራቸው አግዛቸዋለሁ።

ከጓደኞቼ ጋር ደስተኛ ነኝ።

ስህተታቸውን ሁሉ ይቅር እላለሁ።

ከጓደኞቼም ጋር አልጣላም።



ከጓደኞቼ ጋር እጫወታለሁ።

ለወንድሞቼ ፣ ለእህቶቼ እና ለጓደኞቼ ትንሽየ ስጦታዎችን እሰጣለሁ።

ወንድሞቼን እና እህቶቼን እወዳቸዋለሁ።

ከእነሱም ጋር አልጣላም።


መጫወቻዎችን እና አሻንጉሊቶችን ከጓደኞቼ ፣ ከወንድሞቼ እና ከእህቶቼ ጋር እጋራለሁ።

ከጓደኞቼ ጋር የማወራው በትህትና ነው።

የማገኛቸው በፈገግታ ነው።

በጓደኞቼ ላይ አልስቅም።

ጓደኛ የምሆነው ከጥሩ ልጆች ጋር ብቻ ነው።



ትምህርት 19

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)

አንድ ትንሽ ልጅ ነበር። ስሙ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ነው። የአባቱ ስም አብደላህ ነው። የእናቱ ስም ደግሞ አሚና ነው። አባቱ የሞተው ከመወለዱ በፊት ነበር። እንዲሁም ህጻን እያለ እናታቱ ሞተች። ከዚያም አያታቸው ተንከባክቦ አሳደገው።

አያቱ ከሞቱ በኋላ አጎታቸው ተንከባክቦ ልክ እንደ ልጁ አድርጎ አሳደጋቸው። የአያታቸው ስም አብዱል ሙጦሊብ ነበር፤ የአጎታቸው ስም ደግሞ አቡ ጣሊብ ነበር።

ይህ ትንሽ ልጅ በጣም ጥሩ ልጅ ነበር። ሁልጊዜ እውነት ይናገር ነበር። ስለዚህ ሁሉም ሰው "አስ-ሷዲቅ" (እውነተኛው) ብለው ይጠሩት ነበር። በጣም ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ሁሉም "አል-አሚን" (ታማኙ) ብለው ይጠሩት ነበር።

ይህ ልጅ በኋላ ላይ የአላህ ነብይ ሆነ። ነብይ ማለት የአላህ መልእክተኛ ማለት ነው።



ትምህርት 20

መልካም ሥራዎች

መልካም ሥራዎች ማለት ጥሩ ተግባራት ማለት ነው።

ሳንቲሞችን ካሳፎርቶ ውስጥ እናስቀምጣለን አይደል?

አዎ ሳንቲሞችን ካሳፎርቶ ውስጥ እናስቀምጣለን።

ካሳፎርቶ ወይም ሳጥን ውስጥ ብዙ ሳንቲሞች አሉ። ሳጥኑ ሙሉ ነው። መልካም ስራዎችን እንሰራለን። በጎ ተግባራትን እንፈፅማለን። በጎ ተግባራትን የምንሰበስበው ልክ እንደ ሳንቲሞቹ ነው። ሁልጊዜ መልካም ስራዎችን መስራት ይኖርብናል።

የመልካም ስራዎችን ሳጥን ማየት አንችልም። ሳጥኑ ሙሉ ነው።

መልካም ስራዎች ምንድን ናቸው?

የሚከተሉት የተወሰኑ መልካም ሥራዎች ናቸው፡

1. አላህን መታዘዝ
2. በየቀኑ አምስት ጊዜ መስገድ
3. ቁርአን መማርና ማጥናት
4. አላህን መውደድ እና መታዘዝ አለብን

5. ነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) መውደድ እና መታዘዝ
6. ወላጆቻችንን፣ ወንድሞቻችንን እና እህቶቻችንን መውደድ
7. ሰዎችን መርዳት
8. ትምህርታችንን በደንብ ማንበብ
9. ወላጆቻችነን እና መምህራችነን ማክበር እና መታዘዝ
10. ከሁሉም ሰው ጋር ተግባቢ መሆን አለብን



ትምህርት 21

እንግዶቼ

እንግዳ እወዳለሁ።

እንግዳ ሲመጣ ደስተኛ ነኝ።

እንግዳ የምቀበለው በፈገግታ ነው።

እንግዳ ሲመጣ መጀመሪያ ሰላም እለዋለሁ። ከዛም እንዲቀመጥ እጠይቀዋለሁ።

አከብረዋለሁ። እንዴት ነህ? ብየ እጠይቀዋለሁ።

ቤት ውስጥ ያለውን ቆንጆ ምግብ አቀርብለታለሁ።



ከእሱም ጋር ደስብሎኝ አወራለሁ።

ደስ ብሎት ጊዜውን እንዲያሳልፍ የቻልኩትን እጥራለሁ።

እንግዳየን በደንብ አስተናግደዋለሁ።

የሶላት ሰአት ሲደርስ ውዱእ የሚያደርግበትን ውሃ አዘጋጅለታለሁ።



ምግብ ከመብላቱ በፊት እና ከበላ በኋላ እጁን አስታጥበዋለሁ።

ከቤተሰቦቹ እና ከታላላቆቹ ጋር ሲያወራ ንግግራቸውን አላቋርጥም።

እንግዳየን እወዳለሁ።

ትምህርት 22

ጎረቤቴ

ጥሩ ጎረቤት አሉኝ።

የሚኖረው ከእኛ ቤት ጎን ነው።

ትህትና አሳየዋለሁ።

ባየሁት ቁጥር ሰላም እለዋለሁ።

አንዳንድ ጊዜ ምግብ አብረን እንበላለን።

ስጦታም እሰጠዋለሁ።ትንሽም ቢሆን ስጦታየን ይወደዋል።

ወደ ቤት እንዲመጣ እጠይቀዋለሁ።

እኔም ወደ ቤቱ እሄዳለሁ።



በስራው አግዘዋለሁ። እሱም ያግዘኛል።

ሲታመም ቤቱ ሄጀ እጠይቀዋለሁ።

ከእሱ መልካም ነገሮችን እማራለሁ፤ መልካም ነገሮችንም
አስተምረዋለሁ።

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ "ጎረቤቱ ከእሱ ተንኮል (ክፋት)
ሰላም ያልሆነ ሰው ጀነት አይገባም።"

ትምህርት 23

መመለስ ትችላለህ?

ጥያቄ፡ አላህ ማነው?

መልስ፡ አላህ አንድና ብቸኛ ነው።

ጥያቄ፡ አላህ ልጅ ወይም ቤተሰብ አለው?

መልስ፡ የለም፣ አላህ ልጅም ሆነ ቤተሰብ የለውም።

ጥያቄ፡ ይህንን ዓለም ማን ፈጠረው?

መልስ፡ ይህንን ዓለም የፈጠረው አላህ ነው።

ጥያቄ፡ ማምለክ እና መታዘዝ ያለብን ማንን ነው?

መልስ፡ ማምለክ እና መታዘዝ የለብን አሏህን ብቻ ነው።

ጥያቄ፡ ሌላ ስለ አሏህ ምን ታውቃለህ?

መልስ፡ አላህ አንድ ነው። ሃያል ጥበበኛ ፣ አዛኝ መሃሪ ነው።

ጥያቄ፡ አላህን መታዘዝ አለብን

መልስ፡ አዎ አላህን መታዘዝ አለብን።

ጥያቄ፡ አላህን እንዴት ትታዘዛለህ?

መልስ፡ ቁርአንን እና የነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) መንገድ በመቀበል እና በመከተል አላህን እታዘዛለሁ።

ጥያቄ፡ አላህ እንድትከተሉት ያስገድዳችኋል?

መልስ፡ አላህ እሱን እንድንከተል አያስገድደንም።

ጥያቄ፡ እንዴት ሰላም ማግኘት እንችላለን?

መልስ፡ እስልምናን በመከተል ሰላምን ማግኘት እንችላለን።

ጥያቄ፡ ስኬታማ እንዴት መሆን ትችላላችሁ?

መልስ፡ ኬታማ መሆን የምችለው የነብዩ ሙሐመድ ሱና በመከተል ነው።

ጥያቄ፡ ሙስሊም ሰው ሊያምንባቸው የሚገቡ ስድስቱን የእምነት መሰረቶች ጥቀስ።

መልስ፡ ሙስሊም በሚከተሉት ያምናል፡

1. በአንድ አላህ
2. በመላእክት
3. በአላህ መጽሐፍት
4. በነብያት
5. ከሞት በኋላ ባለው ህይወት።
6. ጥሩም ይሁን መጥፎ ሁሉም ነገር ሚሆነው በአላህ ውሳኔ ነው ብሎ ማመን ናቸው።

ጥያቄ፡ ኃደኛህን ለማን ብለህ መውደድ አለብህ?

መልስ፡ ኃደኛዬን ለአላህ ብዬ መውደድ አለብኝ።

ጥያቄ፡ ከወላጆቻችሁ ጋር ያላችሁ ምግባር ምን ይመስላል?

መልስ፡ ወላጆቼን እወዳለሁ፤ አከብራለሁ ፣ እታዘዛለሁ። ሁሌም አገለግላቸዋለሁ። ሳወራቸውም በትህትና ነው።

ጥያቄ፡ የጓደኞቻችሁን ወላጆች የምትቀርቧቸው እንዴት ነው?

መልስ፡ የጓደኞቼን ወላጆች እወዳቸዋለሁ፤ አከብረቸዋለሁ።

ጥያቄ፡ የምታወሩት እንዴት ነው?

መልስ፡ የማወራው ቀስ ብየ እና ግልፅ ሆኜ ነው። መጥፎ ቃላቶችን አልጠቀምም። ክፍል ውስጥ የማይረባ ወሬ በትምህርት ጊዜ አላወራም። አልጮህም።

ጥያቄ፡ ምትራመደው እንዴት ነው?

መልስ፡ የምረዳው ረጋ እና ጠንከር ብየ ነው።

ጥያቄ፡ ጓደኛ የምታደርገው ማን ነው?

መልስ፡ ጓደኛ የማደርጋቸው መልካም ልጆችን ብቻ ነው።

ጥያቄ፡ ከአንድ ጓደኛችህ ጋር ብትጣላ ምንድን ማድረግ አለብህ?

መልስ፡ ስህተቴን መቀበል አለብኝ። ይቅርታ እላለሁ። እናም መጣላቴን አቆማለሁ።

ጥያቄ፡ መስጠት ያለባችሁ እንዴት አይነት ስጦታ ነው?

መልስ፡ ስጦታ የግድ ውድ መሆን የለበትም። ጥሩ ነገር መሆን አለበት። ዋናው የእናንተ ውዴታ ነው። መጽሐፍ ፣ አበባ ጥሩ ስጦታዎች ናቸው።

ጥያቄ፡ ጓደኛችሁን የምትወዱት ላማን ስትሉ ነው?

መልስ፡ ጓኞቼን የምወደው ለአላህ ስል ነው።

ጥያቄ፡ እንግዶችን የምትንከባከቡት እንዴት ነው?

መልስ፡ እንግዶቼን በጥሩ ሁኔታ አስተናግዳለሁ። ምርጥ ምግብ እና መጠጥ እሰጣቸዋለሁ። በጥሩ ሁኔታ አናግራቸዋለሁ።

ጥያቄ፡ በጓደኛህ ቤት በእንግድነት ስንት ቀናት ትቆያለህ?

መልስ፡ በጓደኛዬ ቤት በእንግድነት ከ 3 ቀናት በላይ መቆየት የለብኝም።

ጥያቄ፡ ከመምህራችሁ ጋር ያላችሁ ባህሪህ ወይም ግኑኝነት ምን ይመስላል?

መልስ፡ መምህሬን እታዘዛለሁ፤ አከብራለሁ።

ጥያቄ፡ ለአምስቱን የእስልምና መሠረቶች ትርጉም ስጥ።

መልስ፡

1. **ሸሐዳ**: ላኢላሃ ኢለላህ በማለት እምነትን ማወጅ ነው።
2. **ሶላት**: በቀን አምስት ጊዜ መስገድ ነው።
3. **ዘካ**: የድሆች መዋጮ ማለት ነው።
4. **ሰዉም**: የረመዳን ወር መጾም ነው።
5. **ሐጅ**: ወደ መካ በመሄድ ካዕባን መጎብኘት ነው።

ጥያቄ፡ ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) አል-አሚን ተብለው የተጠሩት ለምንድን ነው?

መልስ፡ ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) አልአሚን የተባሉት ታማኝ ስለነበሩ ነው።

ጥያቄ፡ መልካም ሥራዎች ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፡ መልካም ሥራዎች ማለት ጥሩ ተግባራት ማለት ነው።

ጥያቄ፡ መልካም ሥራችንን የሚመዘግበው ማነው?

መልስ፡ መልካም ሥራችንን የሚመዘግቡት መላእክት ናቸው።

ጥያቄ፡ የተወሰኑ የነብያትን ስም መጥቀስ ትችላለህ?

መልስ፡ ነብያት፡- አደም ፣ ኑህ ፣ ኢብራሂም ፣ ሙሳ ፣ ዒሳ (ዐ.ሰ) እና ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው።



ትምህርት 24

እነዚህን ጥያቄዎች መልስ

የሚከተሉትን ቃላት መቼ ትጠቀማለህ?

ቢስሚላህ መቼ ትላለህ?

ሱብሃነላህ መቼ ትላለህ?

ያ አላህ መቼ ትላለህ?

አልሀምዱሊላህ መቼ ትላለህ?

ማሻአላህ መቼ ትላለህ?

አስታግፊሩላህ መቼ ትላለህ?

ፊ አማኒላህ መቼ ትላለህ?

ጀዛከላህ መቼ ትላለህ?

አሰላሙ አለይኩም መቼ ትላለህ?


ትርጉማቸውን ግለጽ፡

የቢስሚላሂር ረህማኒር ረሂም ትርጉም ምንድን ነው?

አላሁአክበር መቼ ትላለህ?

አላሁአክበር ምን ማለት ነው?

አምስቱ የእስልምና መሠረቶች ምንድን ናቸው?



ተጨማሪ ጥያቄዎች፡

ዱዓ ምንድን ነው?

አል-አሚን ተብሎ የሚጠራው ማነው?

መልካም ሥራዎች ምንድን ናቸው?

መልካም ሥራዎችን መሰብሰብ እንችላለን?

አምስቱ የየቀኑ ሶላቶች የትኞቹ ናቸው?

እንዴት ጥሩ ልጅ መሆን ትችላለህ?

